# ዕድሜ ለሀይቲ መልዕክተኛ

የ1949 ዓ.ም የማክሰኞ ግንቦት 17 ዕለት፤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ታሪክ ውስጥ ሊጠቀስ የሚገባ አንድ ድርጊት ሲፈጸም ታይቷል። ይኸውም ኮሎኒያሊስቶችና ኢምፔሪያሊስቶች፣ ሊበራሎችና ካፒታሊስቶች፣ ለግል ጥቅማቸው እርስ በርሳቸው ቢተባበሩና ቢረዳዱም፤ የድሆች አገሮች ሳይፈሩ አንድነታቸውን አጠንክረው ለጋራ አቋማቸው ከተሰለፉ፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ላይ የኃያላኖቹን ፍላጐት ለማክሸፍ የሚችሉ መሆናቸው ነው።

በቀድሞ የጄኔቬ የመንግሥታት ማህበር ዘመን፣ ዳኝነቱ የሚፈጸመው ለታላላቆቹ በሚመች ሕግ ስለነበረ፤ ኢትዮጵያ ያ ሁሉ ግፍ ሲፈጸምባት ፍርድ ይታይላት አልተባለም። በኢትዮጵያ ላይ የደረሰው በደል ትምህርት ሆኖ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ላይ በ1945 ዓ.ም በሚያዝያ ወር፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እንደገና ሲወለድ፤ መብት ለሁሉም እኩል እንዲሆን የመተዳደሪያው ደንብ ቢገልጽም፣ የአንድ ትንሽና የድሀ አገር የተቃውሞ ድምፅ፣ የታላላቆቹን ጥቅም እስከዚህ የሚያበላሽ ይሆናል ተብሎ የታሰበበት አይመስልም። በቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ፤ ግንቦት 17 ቀን 1949 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ሸንጎ የሀይቲ መንግሥት ዋና መልዕክተኛ ሴናተር ሰንት ሎት የወሰደው እርምጃና የደረሰው ሁኔታ ምሳሌነቱ ጠቃሚ ነው።

ሊቢያ በሶስት አውራጃ ተከፍላ፣ ሶስት የአውሮፓ ኮሎኒያሊስቶች፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይና ጣልያን ከአሜሪካ እርዳታ ጋር እያንዳንዱን ክፍለ ሀገር፣ ለአሥር ዓመታት ይዘው እንዲቆዩ ተቀምጦ የቀረበው ሀሳብ፣ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ መጽደቅ ያልቻለው፣ የአንድ ትንሽ የድሀ አገር ወኪል ስለተቃወመና፣ በዚሁ የተነሣ፣ አንድ ድምፅ ስለጐደለ ብቻ ነው።

ሴናተር ሰንት ሎት (ST.LOT) የተባለው የሀይቲ ሬፑብሊክ ዋና መልዕክተኛ፤ ከአገሩ መሪ ከሚስተር ኤስቲሜ ዱ.ማርሴ (ESTIME DU MARSAIS) የተሰጠውን ትእዛዝ ጥሶ የኮሎኒያሊስቶቹን ዕድል ያከሸፈው፣ ጣልያን ወደ ሊቢያ እንዳትመለስ አጥብቀው የሚቃወሙት የዓረብ አገሮች በገንዘብ ገዝተውት ነው ተብሎ በሰፊው ታምቷል። የሀይቲው ዋና መልዕክተኛ ይህንን ከፍተኛ እርምጃ የወሰደው፤ እንደ ሐሜታው በገንዘብ ተደልሎም ከሆነ፣ የተገዛው በኮሎኒያሊስቶቹ ሳይሆን እነሱን የሚቃወሙ በመልማት ላይ በሚገኙ አገሮች ስለሆነ፣ ወገኖቹን ለመጉዳት ያደረገው ኃጢአት የለም። ወይም ደግሞ ጉቦ ሳይቀበል ለድሆች ሕዝቦች የመቆርቆር ስሜቱ ገፋፍቶት የወሰደው እርምጃ ከሆነ፣ ላስገኘው ውጤት በሊቢያ ምድር አንድ ሀውልት እንዲቆምለት ያስፈልግ ነበር። የዚህ ሰው ተቃዋሚነት ባልተጠበቀ መንገድ በድንገት ብቅ ባይል ኖሮ፣ ሊቢያ በሶስት ኮሎኒያሊስቶች ተከፋፍላ ቢያንስ ለአሥር ዓመታት የቅኝ አስተዳደርን እፍዳ ትቀበል ነበር። <u>በተለይም ያ እንደዚያ ከጣልያን እጅ አስጥሉን እያለ ጩኸቱን ያሰማው የትሪፖሊታንያ ሕዝብ፤ የሮማ መንግሥት ተመልሶ እንዳይገባበት በሩን የዘጋለት፣ የሀይቲ ዋና መልዕክተኛ መሆኑን ታሪክ ሊያስታውሰው ይገባል።</u>

የታሰበው ይበላሽብኛል ብሎ ያልጠበቀው የጣልያን መንግሥትና ሕዝብ፤ መራራው ዜና ሲደርሰው እውነት ነው ብሎ መቀበል ጨርሶ አልቻለም። ጣልያኖች ችኩል በሆነው መንፈሳቸው ገና ከመጀመሪያው፤ ኧርነስት ቤቨንና ካርሎ

ድምፃቸውን ሲሰጡ፣ ኤርትራንም አብረው እንዲደግፉ እኛ በጠየቅናቸው መሠረት የተፈጸመ ነው ....... » ብኋል::

ስፎርሳ የተናገረው ሀሰት አይደለም:: የጣልያን መንግሥት ትሪፖሊታንያ እና ሱማሌ እንዲመለሱለት፣ ከወዳጆቹ ከላቲን አሜሪካ አገሮች የሚያገኘው ድጋፍ፤ የኤርትራንም ጉዳይ እንዲጨምር የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት የሚጠይቅ ስለሆነ፣ ግንቦት 17 ቀን በጠቅላላው ጉባኤ ላይ የተካሄደው የድምጽ አሰጣጥ፣ ስፎርሳ እንደተናገረው መፈጸሙ እውነት ነው:: ይህም የተደረገው ኢትዮጵያን ለመርዳት ተፈልጐ ሳይሆን፣ ትሪፖሊቻንያን እና ሱማሌን ለጣልያን ለመዳረግ፣ ለኤርትራም የቀረበው መፍትሔ አብሮ ከመጽደቅ በስተቀር ሌላ ምርጫ ስላልነበረ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ የኤርትራ ጉዳይ ደንቡ ከሚጠይቀው ከሁለት ሶስተኛው ድምፅ የበለጠ ቁጥር ለማግኘት የቻለው፣ በሮማ መንግሥት ወዳጆች ምክንያት ብቻ ሳይሆን፣ በኢትዮጵያ መልካም የፖለቲካ አቋም፤ ከዓረብ አገሮችም በተገኘው ድጋፍ መሆኑ መረሳት የለበትም::

በዚያን ዘመን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሚካሄደው፤ እንደነ አርጀንቲና የመሳሰሉት አገሮች በሚፈጽሙት የማወናበድ ዘዴ ባይሆን ኖሮ፤ ደንቡ የሚጠይቀውን ከፍተኛ የድምፅ ብልጫ ያገኘው የኤርትራ ጉዳይ ጸድቆ፣ ሌሎቹ ያልተሟላላቸው የሊቢያና የሱማሌ ጉዳዮች በቀጠር ሊተላለፉ በተገባ ነበር:: ነገር ግን እኔ ከሞትኩ ስርዶ አይብቀል እንደተባለው፣ የጣልያን ዕድል በመሰናከሉ፤ የኤርትራ ጉዳይ ለብቻው ውሳኔ እንዲያገኝና ኢትዮጵያ እንድትደሰት ስላልተፈለገ፣ የሁሉም ጉዳይ ለመስከረም 1949 ዓ.ም እንደገና እንዲታይ በቀጠሮ ተላለፈ::

## ጥሩው ዕድል አመለጠ::

« ጥሩው ዕድል አመለጠ » የሚለውን ቃል የተጠቀመው፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የታላቋ ብሪታንያ የመልዕክተኞች መሪ፣ የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት ሳይጸድቅ የቀረበትን ምክንያት ለማስረዳት ባቀረበው ራፖር ነው::

በንዑስ ኮሚቴ «15» እና በዋናው ኮሚሲዮን ጸድቆ፣ ለጠቅላላው ጉባኤ የመጨረሻ ውሳኔ የቀረበው የቀድሞዎቹ የጣልያን ኮሎኒዎች መፍትሔ፣ ሁለት ሶስተኛውን የአባል አገሮች የድጋፍ ድምፅ እንዲያገኝ፣ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት መልዕክተኞች ያደረጉት ድካም ወሰን አልነበረውም::

የዓረብ መንግሥታት ከእስላም አገሮች ጋር ሆነው፣ በጣልያን ላይ የነዙት የጥላቻ ንግግር የሚገርክ በመሆኑ፤ በዋናው ኮሚሲዮን ላይ ድጋፋቸውን የሰጡ፣ ወይም አብስቴንሽን ያደረጉ አንዳንድ አገሮች፣ ጠቅላላው ጉባኤ ላይ ሲቀርቡ፣ በተለይ በትሪፖሊታንያ እና በሱማሌ ጉዳይ አቋማቸውን መለወጥ ፈለጉ:: የኤርትራ፣ የሲሬናይከም ሆነ የፌዘን ጉዳይ አላሳሰባቸውም:: ይልቁንም ኤርትራን የሚመለከተው ክፍል፣ ኢትዮጵያ ከዓረብ አገሮችም ድጋፍ ስለቀረበላት፣ ከሁለት ሶስተኛው ቁጥር የበለጠ ድምፅ አግኝታ ነበር:: ትልቁ ችግር በጣልያን ላይ ያለው ጥላቻ በመሆኑ፣ እንግሊዞች ያላቸውን ኃይል በሙሉ በመጠቀም ብዙ ጥረት ቢያደርጉም፣ በትሪፖሊታንያ ጉዳይ ሳይታሰብ በድንገት የተፈጠረው፤ የሀይቲ መልዕክተኛ ተቃውሞ አንድ ድምፅ ስለአስጐደለ ውሳኔው ወደቀ::



ኧርነስት ቤቨን የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እና ረዳቱ ሄክቶር ሜክኒል ሚኒስትር ዴታ፣ በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ፣

(ግንቦት 1949 ዓ.ም)

« ....... የቅኝ ግዛቶቹ ጉዳይ ያ ሁሉ ድካም ተደርጉበት መጨረሻው ሳያምር የቀረው፣ በጣልያን መንግሥት በኩል የተነዙት ፍሬቢስ ፕሮፓጋንዳዎች ባመረቱት ውጤቶች ነው። ለችግሩ መፍትሔ እንዲሆን፣ ኮምት ስፎርሳና እኔ ተወያይተን የተስማማንባቸው መሠረታዊ ቁም ነገሮች፣ በይፋ ተገልጠው የፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ እንዲሆኑ ማድረግ አይገባም ነበር። ...... በትሪፖሊታንያ እና በሱማሌ፣ ጣልያን እንዲመለስ ስምምነት ስለተገኘ፣ በቅርቡ አስተዳዳሪዎቻችሁ ይመጡላችኋል ...... እየተባለ፣ በራዲዮ የተነዛው አጉል ፕሮፓጋንዳ፣ ሕዝቡ በጣልያን ላይ ያለውን የጥላቻ ስሜት በከፍተኛ ሁኔታ ስለአገነፈለው፣ የዓረቦችንና የእስላም አገሮችን ተቃውሞ አስተባበረ። በተለይ የዓረብ አገሮች፣ ታላቋ ብሪታንያ፣ ትሪፖሊታንያን ለጣልያን መልሳ ለመስጠት በመዶለቷ አናዝናለን በማለት፣ ከፍ ያለ ቅሬታ አድርባቸዋል። ....... » በብዙ ድካም ተቀነባብሮ ለተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ የቀረበው ውሳኔ የወደቀበትን ምክንያት፣ ከዚህ በላይ በተገለጸው አኳኋን ካስረዳ በኋላ፣ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሀሳቡን ሲዘጋ፣ « ...... <u>ከእንግዲህ ወዲህ በእኔና በኮምት ስፎርሳ መካከል የተደረገው ስምምነት፣ ሞቶ፣ ቀብሩ ተፈጽሟል</u> ...... » ብሏል።

# የጃንሆይ አመለካከት

*« ..... ስለ ኤርትራ ዋና ገዳያችን ይኸ የቤቨን ስፎርሳ መስማማት በተባለው ነገር ልባችን ሙሉ በሙሉ አለመደሰቱን ታውቃለህ። ሆኖም ግማሹን እጃችን አድርገን፣ ሌላውን ወደፊት መታገል ይበጃል ብለህ ያቀረብከውን ሀሣብ ተመልክተን፣ እንድትገፋበት ፈቅደንልሃል ...... »*

*ቀ.ኃ.ሥ ግንቦት 12 ቀን 1949 ዓ.ም*

ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን የንጉሠ ነገሥቱን መሪ ቃል አቶ አክሊሉ ደህና አድርገው ያስታውሳሉ። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሙሉ በሙሉ ባይደሰቱም፣ ኢትዮጵያ በግንቦት ወር 1949 ዓ.ም የቤቨን ስፎርሳን ፎርሙላ ከመቀበል በስተቀር ሌላ ምርጫ አልነበራትም። ይሁን እንጂ በጃንሆይ አካባቢ የሚተራመሱ ልዩ ልዩ ሀሳቦች ነበሩ።

– የአቶ አክሊሉን ሥራ ለማንኳሰስ፣ አንዳንዶቹ በሚሰነዝሩት ሀሳብ፣ « ..... ኢትዮጵያ በዓለም ዳኞች ፊት የምታቀመው ደህና ጠበቃ ቢኖራት ኖሮ፣ የኤርትራ ግዛት በክርስቲያንና በእስላም ሀይማኖት ተከፋፍሎ እንዲኖር የቀረበውን ሀሳብ ማፍረስ ይቻል ነበር ...... » ብለው ይዳንታሉ።

– ሌሎች ደግሞ፣ « ....... ኤርትራን ለማስመለስ ከእንግሊዞች ጋር የተሳሰረ የወዳጅነት ውል እንዲኖር ያስፈልጋል። ኤርትራን እናንተ በሚመስላችሁ ዘዴ መልሱልን ተብሎ ለእንግሊዞች አደራ ቢሰጣቸው፣ እነሱ ይፈጽሙልን ነበር። አሁን በወልደጊዮርጊስና በአክሊሉ የተያዘው ትልቁ ሥራ፣ ከእንግሊዞች ጋር መቃቃርን ማስፋፋት ስለሆነ፣ ጃንሆይ ብዙ ችግር ወድቆባቸዋል ..... » የሚል ሀሜታ ይነዛሉ።

– በጣም ጥቂቶቹ፣ « ኤርትራን እናስመልሳለን እየተባለ የሚደረገው ሩጫና የሚፈሰው ገንዘብ አለአግባብ ነው። ኢትዮጵያ የባሕር በር ከሌላት

« ...... በቤቨን ስፎርሳ ስምምነት መሠረት፣ ለእያንዳንዱ የቀድሞ የጣልያን ቅኝ ግዛት፣ የተዘጋጀው መፍትሔ ለጠቅላላው ጉባኤ ሲቀርብ፣ የኤርትራ ጉዳይ ብቻውን በጣም ከፍተኛ የሆነውን (ከሁለት ሶስተኛ ቁጥር በላይ) የድጋፍ ድምፅ አግኝቶ ነበር። ነገር ግን ለሊቢያና ለሱማሌ የተዘጋጁት መፍትሔዎች፣ ደንቡ የሚጠይቀውን የሁለት ሶስተኛውን የድጋፍ ድምፅ ባለማግኘታቸው፣ የቀድሞዎቹ የጣልያን ኮሎኒዎች ጉዳይ በጠቅላላው የኤርትራም ጭምር፣ በመጭው መስከረም ወር በሚከፈተው፤ በአራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ ውሳኔው እንዲሰጣቸው በቀጠሮ ተላልፈዋል።

..... ይህ ሊደርስ የቻለው በትሪፖሊታንያ እና በሱማሌ ጉዳይ፣ በዋናው ኮሚሲዮን ውሳኔዎቹን የደገፉ አንዳንድ አገሮች፣ በጠቅላላው ጉባኤ ላይ፣ ሀሳባቸውን ለውጠው ወደ ተቃዋሚነት በመዛወራቸው ነው።

ይኸውም፣ 1ኛ/ በሊቢያ ጉዳይ ትሪፖሊታንያ ለጣልያን እንዳይሰጥ፤ የሀይቲ መልዕክተኛ ከመንግሥቱ መሪ የተሰጠውን ትእዛዝ ጥሶ፣ ዓረቦቹን ለመደገፍ ድምጹን በመለወጡ ሲሆን፣ 2ኛ/ በሱማሌ ጉዳይ ደግሞ ላይቤሪያና ሕንድ ከእኛ ጋር ሆነው ጣልያንን በመቃወማቸው ነው።

ለኢትዮጵያ ከፍተኛውን ድጋፍ ያገኘው የኤርትራ ጉዳይ፤ ከሌሎቹ ተለይቶ ለብቻው እንዲጸድቅ፣ አብዛኛዎቹ የመንግሥታት አባሎች ባለመስማማታቸው፤ ለመስከረም እንዲተላለፍ የተሰጠውን ቀጠሮ ከመቀበል በስተቀር ሌላ ማድረግ አልቻልንም። ....... በደረሰው ሁኔታ ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን፣ እንግሊዞችም ብዙ የለፉበትን፤ የሲረናይከን አውራጃ ባለማግኘታቸው በጣም አዝነዋል። አሜሪካኖቹም እጅግ ተገርመዋል። በልማዱ፤ በዋናው ኮሚስዮን ላይ ስምምነት ተገኝቶ የተወሰነ ጉዳይ፤ ጠቅላላው ጉባኤ ላይ ሲደርስ፣ እክል ይገጥመዋል ተብሎ አይታሰብም ነበር።

...... የኤርትራ ጉዳይ ከፍተኛውን የድጋፍ ድምፅ ሲያገኝ፣ ጣልያን ወደ ትሪፖሊታንያም ሆነ ወደ ሱማሌ እንዳትመለስ ስለታገደች፣ ንዴት ብቻ ሳይሆን ሀፍረትም አድሮባታል። ወዳጆቿ ፈረንሣይና የላቲን አሜሪካ አገሮችም፤ የጣልያን ግፈር የእነሱም ጭምር ሆኖ ስለታያቸው፤ ብስጭታቸው ወሰን አጥቷል። ዓረቦቹና የእስላም አገሮች፤ በትብብራችን ጣልያንን ድል አደረግን ብለው፣ ከመጠን በላይ ተደስተዋል። ሶቪየት ሕብረትና ወገኖቹ፣ በእነሱ ተቃዋሚነት የእንግሊዝና የአሜሪካ ጥቅም ታገደ በማለት በሰፊው ፎክረዋል።...... በኒውዮርክ የተመደብነው የኢትዮጵያ መልዕክተኞች፤ ከጃንሆይ የተሰጠንን መምሪያ ተከትለን የተቻለንን ሁሉ የፈጸምን ይመስለኛል። በተባበሩት መንግሥታት ያደረግነው ሙግት፣ በኤርትራ ጥያቄያችን ከፍተኛውን ድጋፍ አግኝቶልን ነበር።ሳይጸድቅልን የተላለፈው በሌሎች ምክንያት ነው። አሁንም ቀጠሮአችን ለመስከረም ስለሆነ፣ ከዚያ በፊት ማድረግ የሚገባንን ፕላን አዘጋጅቼ፤ አዲስ አበባ እንደተመለስኩ ለጃንሆይ አቀርባለሁ። የጃንሆይ መልካም ፈቃድ ቢሆን፤ ወደ አዲስ አበባ ስመለስ እግረ መንገዴን ሎንዶን ላይ ቆሜ፤ ለመስከረም ስለተቀበልነው ቀጠሮ፤ ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር ለመነጋገር አስቤአለሁ። ...... »

አክሊሉ ሀብተወልድ በሶስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ስብሰባ ላይ፣ ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች መፍትሔ የወሰዱት አቋም፣ ልዩ

ብሪታንያ መልዕክተኛ ጋር፣ አቶ አክሊሉ ጥሩ መግባባት ፈጥረው በሕብረት ሠርተዋል ወይ ? የሚለው ጥያቄ፣ መልስ የሚጠብቅ መሆኑ ግልጽ ነው።

አዲስ አበባ ያለው የእንግሊዝ አምባሳደር ዳንኤል ላሴል (DANIEL LASCELLES) ከግንቦት 14 ቀን 1949 ዓ.ም ጀምሮ፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ከእንግሊዝ መልዕክተኛ ጋር በቅርብ እየተባበሩ እንዲሠሩ፤ ከንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ

ተላልፎላቸዋል እያለ በቴሌግራም ለሎንዶንና ለኒውዮርክ እየደጋገመ ይገልጽ ነበር። ቀጥሎም አክሊሉ ሀብተወልድ በተሰጣቸው ትእዛዝ መሠረት እንዴት አድርገው እንደሚሠሩ በአስቸኳይ ይገለጽልኝ እያለ ይወተውት ነበር። *

በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘንድ የታላቋ ብሪታንያ አምባሳደር ዳንኤል ላሴል፤ አዲስ አበባ በኖረበት ዘመን ለአቶ አክሊሉ ቅን መንፈስ አልነበረውም። በአምባሳደሩ አስተያየት በታላቋ ብሪታንያ እና በኢትዮጵያ መካከል ላለው ግንኙነት፣ አስቸጋሪዎቹ (ወይም እንቅፋቶቹ) ወልደጊዮርጊስና አክሊሉ ሀብተወልድ ናቸው። በሶስተኛው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፤ የቀድሞዎቹ የጣልያን ኮሎኒዎች ጉዳይ እንደታሰበው ሳይፈጸም የቀረው፣ በአቶ አክሊሉ አለመተባበር መሆኑን በኒውዮርክ ያለው የእንግሊዝ መልዕክተኞች መሪ በጽሑፍ ቢያስታውቅ፤ ንጉሠ ነገሥቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸውን እንዲለውጡ ማድረግ ይቻላል ብሎ ያልማል። በኢትዮጵያ ካሉት የተማሩ ወጣቶችም ውስጥ፤ አቶ ይልማ ዴሬሣ ከገንዘብ ወደ ውጭ ጉዳይ ቢዛወሩ ጥሩ ዕድል ነው ብሎ ያምናል። ምስኪን ላሴል፤ በኢትዮጵያ ጉዳይ ይልማ ዴሬሣም ቢሆኑ፣ በእንግሊዞች ላይ ከፍ ያለ ቅሬታ ስላላቸው፤ የሚበገሩ አለመሆናቸውን አያውቅም። አቶ አክሊሉን ከውጭ ጉዳይ ለማስነሳት ይረዳኛል ብሎ ከሎንዶን የሚጠብቀው ደብዳቤ፣ ሰኔ 4 ቀን 1949 ዓ.ም በመካከለኛው ምሥራቅና በአፍሪካ ጉዳይ ዲሬክተር በሚስተር ክሉተን "CLUTTON" ተፈርሞ የተላከለት ቃል የሚከተለው ነበር።

« ..... አክሊሉ ከእኛ ጋር እየተመካከረ እንዲሠራ ከንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ የደረሰው ወይም ያልደረሰው መሆኑን ማወቅ አልቻልንም። አክሊሉ ላይ ያየነው መንፈስ፣ ያው እንደ ድሮው እራሱ አየወሰነ የሚሠራ መስሎ ነው። ሆኖም በጉባኤው ሥራ ላይ ከእንግሊዝ መልዕክተኞች ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖር አድርጓል። ለምሣሌ በትሪፖሊታንያ ጉዳይ፣ በመቃወም ፋንታ የአብስቴንሽን ድምፅ ብትሰጥ ይረዳናል ብለን የጠየቅነውን ፈጽሞልናል። ..... ስለ አክሊሉ ጉዳይ ከአሜሪካ መልዕክተኞች ጋር ስንነጋገር የተስማማነው አንድ ነገር አለ። እስካሁን ድረስ አክሊሉ በየስብሰባው ላይ፣ የሚገልጻቸው አስተያየቶችና የሚወስዳቸው አቋሞች፣ የአገሩን ክብር ለመጠበቅ በብሔራዊ ስሜቱ ስለሆነ፣ እኛ የምንፈልገውን ሁሉ ባለመከተሉ፣ ልንወቅሰው አይገባም ብለናል። ከዚሁ ጋር ደግሞ በእንግሎ አሜሪካኖች ላይ፤ አክሊሉ ከፍ ያለ ጥላቻ አለው እየተባለ የሚነፍሰውን ወሬ

* « .... SHOULD BE GRATEFUL TO LEARN HOW AKLILU APPEARS TO INTERPRET HIS INSTRUCTIONS ..... » (FO 371-7387)

ማስቀየም ባይፈልጉም፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራቸው ከእንግሊዞች መምሪያ እየተቀበለ ይሥራ ይላሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም::

አቶ አክሊሉ፣ በዚህ በሉንዶኑ ጉብኝታቸው ቤቨንና ሚክኒል ያደረጉላቸው አቀባበል የሞቀ ሆኖ ስለአገኙት ይህችን መልካም አጋጣሚ ልጠቀምባት ብለው፣ በመስከረም 1949 ዓ.ም በሚከፈተው የተባበሩት መንግሥታት አራተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፣ ስለ ኤርትራ ጉዳይ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት አቋም ለውጥ ይኖረዋል ወይ ? ብለው ጠየቁ:: « ... የታላቋ ብሪታንያ የግርማዊ ንጉሥ መንግሥት፣ በኤርትራ ጉዳይ የእስልምና ሀይማኖት ከተስፋፋበት ከምዕራብ አውራጃ በስተቀር፣ ሌላው በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሀድ የተስማማበትን ሀሳብ እስከ መጨረሻው ይደግፋል ...... » በማለት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩና ምክትሉ የሚያበረታታ ቃል ሰጥተው ሸኟቸው::

የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ የሉንዶኑን ጉብኝት ፈጽመው አዲስ አበባ ሲገቡ፣ የተደረገላቸው የሞቀ አቀባበል ያልጠበቁት ነበር:: አንድ ጊዜ በታህሣሥ ወር 1967 ዓ.ም በደብረዘይት የዕረፍት ቤታቸው ሆነው፣ ስለዚሁ ጉዳይ አንስተው ትዝ የሚላቸውን ሲተርኩ፣ አክሊሉ ሀብተወልድ እንዲህ አሉ:: « ..... አዲስ አበባ የገባሁት በሰኔ (JUNE) መጨረሻ 1949 ዓ.ም ነበር:: አውሮፕላኑ ቆሞ በሩ ከመከፈቱ በፊት በመስኮት ስመለከት፣ ሊቀበሉኝ ከመጡት ታላላቅ ሰዎች መካከል፣ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ እና አቶ መኰንን ሀብተወልድ፣ እጅ ለእጅ ተያይዘው እየተሳሳቁ ሲጨዋወቱ አየሁ:: የጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ አውሮፕላን ጣቢያ መገኘት እንግዳ ነገር አልሆነብኝም:: ከፍተኛ የሥራ ጉዳይ፣ ወይም የጤና ዕክል ካላጋጠማቸው በስተቀር፣ ሁልጊዜ ይሸኙኛል ብዙ ጊዜም ይቀበሉኛል:: አዲስ ነገር የሆነብኝ የአቶ መኰንን መጨመር ነው:: ለመልዕክት ወደ አውሮፓም ሆነ ወደ አሜሪካ በምሄድበት ጊዜ አልፎ አልፎ ይሸኙኝ እንደነበረ ትዝ ቢለኝም፣ በምመለስበት ጊዜ ሲቀበለኝ አላስታውስም:: በተለይ አሁን የኤርትራ ጉዳይ ባለመወሰኑ፣ ይኽ ቀረ ይኽ ጐደለ፣ የሚል ሙግት ተዘጋጅቶ የሚጠብቀኝ ቢሆን ኖሮ፣ ወይም ደግሞ ጃንሆይ የኔን ወደ አዲስ አበባ መመለስ የሚጠብቁት በቁጣ መንፈስ ቢሆን ኖሮ፣ አቶ መኰንን አውሮፕላን ጣቢያ ሊቀበለኝ አይመጣም ነበር ብዬ አሰብኩ:: ስለዚህ በጃንሆይ በኩል የሚጠብቀኝ መጥፎ ነገር አለመኖሩ ገብቶኝ፣ ከተሳፈርኩበት አውሮፕላን በጥሩ መንፈስ ወርጄ፣ ከብዙ ወራት በኋላ የአገሬን መሬት ረገጥኩ:: ...... በቀጥታ ወደ ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ሄጄ እጅ ከነሣሁ በኋላ፣ ጃንሆይ በቆይታ ለአንድ ሰዓት አነጋገሩኝ:: ከዚያም በመሰብሰቢያው አዳራሽ፣ አልጋወራሹ፣ ጳጳሱ አቡነ ባስልዮስ፣ ራስ ካሣ፣ ልዑል መኰንን፣ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ፣ አቶ ተፈራወርቅና አቶ ገብረወልድ ባሉበት፣ በእነዚህ በአራት ወራቶች ውስጥ፣ በኒውዮርክ የኤርትራ ጉዳይ በምን አኳኋን እንደተካሄደ ከሁለት ሰዓት በበለጠ ጊዜ በረዥሙ አስረዳሁ:: <u>ጃንሆይ እየደጋገሙ የሚጠይቁኝ ለትሪፖሊታንያ አብስቴንሽን ማድረጋችንና በሱማሌ ጉዳይ ተቃዋሚነታችን ምን ጥቅም አመጣልን ?</u> እያሉ ነበር:: ይህንንም ጥያቄ የደጋገሙልኝ ከእንግሊዝ አምባሳደር በቀረበላቸው ራፖር መሠረት መሆኑ ገባኝ:: እኔም በተቻለኝ የእንግሊዞች ዋና ጥረት መጀመሪያ ለራሳቸው ጥቅም መሆኑን እየደጋገምኩ ካስረዳሁ በኋላ፣ <u>በዓለም ጉባኤ ላይ በትሪፖሊታንያ እና በሱማሌ ጉዳይ የጣልያን ደጋፊዎች ሆነን ብንታይ፣ ጃንሆይ የሚደክሙላት ኢትዮጵያ ምን ያህል ውርደት ላይ እንደምትወድቅ፣ መለካት አይቻልም ነበር አልኳቸው::</u> ከዚሁም ጋር አያይዤ የዓረቦችንና የእስላም አገሮችን ጠላትነት ማትረፍ ብዙ ጉዳት ላይ እንደሚጥለን ስገልጽላቸው፣ የሠራሁት ሁሉ ያለ

ሁለተኛ፤ ጠላታችን ጣልያን እንኳንስ አጠገባችን ሱማሌ ላይ ቀርቶ፣ ሩቅም ቢሆን ትሪፖሊታንያ ላይ ዝር እንዳይል፣ አጥብቆ መከላከል ከኢትዮጵያ የሚጠበቅ ግዳጅ ነው ብዬ አምናለሁ:: ይህንን መሠረታዊ የሆነ እምነታችንን ለውጠን፤ ጣልያን እንደገና እንሰራርቶ በተለይ ድንበራችን ሱማሌ ላይ እንዲነግሥ ድጋፍ መስጠት፣ በእኔ ግምት ኢትዮጵያ እንደገና እንድትወረር መንገዱን ማዘጋጀትና፣ ለአገራችን ነፃነትና ክብር የሞቱትን የአባቶቻችንን ታሪክ ማዋረድ ነው::

ሶስተኛ፣ የኢትዮጵያ ዋና ዓላማ የግዛት ማስፋፋት ጉዳይ ሳይሆን፣ ታሪክን እቦታው ለመመለስ፣ ተለያይተው የኖሩትን ሕዝቦች ለማገናኘት ነው ተብሎ ተደጋግሞ ተነግሯል:: ነገር ግን ለጊዜው መፍትሔ ይሆናል በተባለው በቤቨን ስፎርሳ ስምምነት መሠረት፣ የኤርትራን ግዛት በከፊል ለማግኘት ሲባል ብቻ፤ በተባበሩት መንግሥታት ሸንጐ ላይ፣ ኢትዮጵያ ክብሯን ስታ፤ ድጋፏን ለጣልያን ሰጥታ ቢሆን ኖሮ፤ ለመጭው ታሪካችን ምን ያህል የሚያሳፍር ምዕራፍ እንደምናዘጋጅላት መገንዘብ አለብን::

...... እኔ ይህን ሁሉ ስናገር፤ ከእናንተ ከወዳጆቼና ከወገኖቼ የበለጠ የማስብና የወደፊቲቱን ኢትዮጵያ ጉዳይ አርቄ የምመለከት እኔ ብቻ ነኝ ለማለት አይደለም:: በድምፅ አሰጣጥ ረገድ ከሥራ ጓደኞቼም ሆነ ከሌላው ቦታ፣ የተሰነዘረው አስተያየትና ትችት፤ በተግባር ሊፈጸም የሚችል አልነበረም ብዬ አልከራከርም:: ይሁን እንጂ ሁሉም በየፊናው ይኸ ቢደረግ ኖሮ? ይኸ ቢሆን ኖሮ ? ...... ውጤቱ ያምር ነበር እያለ ሀሳቡን ያመቻቸው፣ የጉባኤው ውጤት ከታየ በኋላ ነው:: ጉዳዩ በቀረበ ጊዜ፣ ለትሪፖሊታንያ አንድ ድምፅ፣ ለሱማሌ የሁለት አገሮች ድምፅ፤ ይጐድላል የሚል ሂሣብ አልተተመነም:: በትሪፖሊታንያ ጉዳይ የሀይቲ መልዕክተኛ የመንግሥቱን መምሪያ ጥሶ፤ ከደጋፊነት ወደ ተቃዋሚነት የተለወጠው ሳይጠበቅ በድንገት ነው:: በሱማሌም ጉዳይ፣ ይኸው በጥባጩ የሀይቲ መልዕክተኛ መደገፉን ትቶ ተቃዋሚ መሆኑ፣ ሕንድም ከአብስቴንሽን ወደ ተቃዋሚነት መዛወሩ ያልታሰበ ዱብዕዳ ነው:: አባል መንግሥታቶች ድምፅ እንዲሰጡ ጥያቄው ከመቅረቡ በፊት፣ የእንግሊዝና የአሜሪካ መልዕክተኞች ብርቱ ክትትል አድርገው፣ ውጤቱ የሚያረካቸው እንደሚሆን እርግጠኞች ነበሩ:: ለምሣሌ በትሪፖሊታንያ ጉዳይ ኢትዮጵያ በመቃወም ፋንታ አብስቴን ብታደርግልን፣ የሁለት ሶስተኛውን የድጋፍ ድምፅ ለማግኘት ዋስትና ይሰጠናል ብለው ስለለመኑን፣ ጥያቄያቸውን ቅር እያለን ተቀብለን ፈጽመናል:: በሱማሌ ጉዳይ ግን ጣልያን ተመልሳ ትግዛ ብላ፤ ኢትዮጵያ በምንም ዓይነት ድጋፍ እንደማትሰጥ እንግሊዝና አሜሪካ በሚገባ ተረድተውላታል::

ለኢትዮጵያ ክብር፣ ለኢትዮጵያ የወደፊት ታሪክ፣ በረዥሙ ማሰብና መጨነቁን ትቶ የጊዜውን ጥቅም ብቻ ተከትሎ፣ ጣልያንን አጨብጭቦ መደገፍ ይሻላል ከተባለ፣ ወቃሾቼ እንደተናገሩት፣ ኤርትራ በከፊል ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል የቀረበው ውሳኔ እንደሚጸድቅ እኔም አልክድም:: ነገር ግን እንዲታወቅልኝ የምፈልገው፤ በሱማሌ ጉዳይ በምንም አኳኋን የጠላታችን የጣልያን ደጋፊ ሆኜ በአገሬ ስም ድምፅ ለመስጠት ጨርሶ የማልሞክረው መሆኑን ነው:: በበኩሌ እስካሁን የሠራሁትና የተሰጠኝንም መምሪያ የተረጐምኩት፣ ለኢትዮጵያ በሚጠቅም መንገድ ነው ብዬ አምናለሁ:: እንግዲህ፣ ለሚወቅሱኝም ሆነ፣ እውነት አለህ ብለው ለሚደግፉኝ፣ ማስረዳት አስፈላጊ ነው ከተባለ፤ ከዚህ የበለጠ ማብራሪያ የለኝም:: ..... »

ከዚህ በላይ የተገለጸውን የአቶ አክሊሉን ዝርዝር ማስረጃ፤ በዚያን ዘመን ወጣት ከተባሉት ሚኒስትሮችና ከከፍተኛ ባለሥልጣኖች መካከል፣ አቶ ይልማ ዴሬሣና አቶ መኰንን ደስታ የሚያረካ ሆኖ ሲቀበሉት፤ እነ ዶክተር አምባዬ ወልደማርያም የሚያጠግብ ምክንያት አይደለም በማለት ነቀፌታቸውን ቀጠሉ። አንዳንዶቹም « ..... ስለ ኤርትራ ጉዳይ ወልደጊዮርጊስና አክሊሉ የሚያቦኩት፣ መቼ ተጋግሮ ገበታ ላይ እንደሚቀርብ አይታወቅም ..... » እያሉ ሲተቹ ከረሙ።

አቶ አክሊሉ በአገር ፍቅር ስሜት እየነደዱ የጠላቶቻችንን እና የአጫፋሪዎቻቸውን ተንኮል በመቋቋም፣ በዓለም ጉባኤ ፊት ያደረጉት ትግል ምን ያህል ከባድ እንደነበረ፤ በዚያን ዘመን የዛሬው የቴክኒዎሎጂ ጥበብ ባለመኖሩ፤ ሥዕሉ ኢትዮጵያ መጥቶ ሊታይና ሊመዘን አልቻለም። ማየትና መስማትም የተለያየ በመሆኑ፣ በተባበሩት መንግሥታት ሸንጐ ላይ፤ ከነ ኮምት ስፎርሳ፣ ከነ ሄክቶር ሜክኒል፣ ከነ ዶክተር አርሴ፣ ከነ ኩቭ ደ ሙርቪል ጋር፤ አቶ አክሊሉ የገጠሙትን ሙግትና ያሳዩትን የሚያኮራ ኢትዮጵያዊነት፣ አዲስ አበባ ያሉት ወዳጆቻቸው ሆኑ ተወዳዳሪዎቻቸው ዓይናቸው ባለማየቱ የጆሮአቸውን ማመን አልፈለጉም። በጠቅላላው በአቶ አክሊሉ ላይ ከየአቅጣጫው ይሰነዘሩ የነበሩት ትችቶች ሠላም የሚነሱ፤ አንዳንዴም ሞራል የሚነኩ ነበሩ። ሳይደግስ አይጣላም እንደሚባለው፤ በዚያች በአስቸጋሪ ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱና ጸሐፊ ትእዛዛቸው፤ የአቶ አክሊሉን ብርቱ ጥረት ስለሚያውቁላቸው፤ <u>ሐምሌ 4 ቀን 1949 ዓ.ም የአስቃ ሀብተወልድ ልጅ፤ ከምክትልነት የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሙሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው ሲሾሙ፣ ለኤርትራ ጉዳይ ከሙሉ ሥልጣን ጋር አሁንም ባለ አደራው እሳቸው መሆናቸው በአፈሲየል ተነገረ።</u>